# በኢትዮጲያ የውርስ ሕግ ውስጥ የሚታዩ ችግሮች እና የመፍትሄ ሃሳቦች

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች:-**

ጋሻዬመረሳ

ሕሊናመኮንን

ኖህ ግርማ

ኤፍሬም ታደሰ

ሰላማዊት ሰይፉ

1. በተለያዩ ሕጎች ውስጥ የሚገኙ ድንጋጌዎች የማጣጣም ስራ በመስራት ግልፅ እና ቀጥተኛ እንዲሆኑ ማድረግ በጉዳዩ ዙሪያ እየተነሱ ላሉ ክርክሮች ፍትሃዊ መፍትሄ ከመስጠትም በዘለለ የአገሪቱን የሕግ ሥርዓት ወጥና ተገማች ለማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

2. የሟችን ዋና መኖሪያ ስፍራ ለሟች ውርስ መክፈቻነት መጠቀሙ የተሻለና ህጉን የበለጠ የሚያብራራው በመሆኑ የህጉ ድንጋጌ በዚሁ መልክ ቢሻሻል መልካም ነው::

3. በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 837 ውስጥ የተመለከቱት ፆታ፣ ዕድሜ እና ዜግነት' በወራሽነት መብትን በተመለከተ ምንም ልዩነት እንደማይፈጥሩና እንቅፋት እንደማይሆኑ የተጠቀሱ ናቸው። የጤና ሁኔታ፣ አካል ጉዳት፣ ዘር፣ ብሄር፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ አቋም በማከለ ሁኔታ ቢቀመጥ ይሻላል።

4. ለውርስ ያልተገባ ስለመሆን በሕጋችን ለውርስ ያልተገባ ሊያደርጉ የሚችሉ ሁኔታዎችን ሲያስቀምጥ ድርጊቶቹ ተፈጽመዋል የሚሉና መፈፀማቸውን የሚያሳዩ ወራሾች እስከ መቼ ማሳወቅ እንዳለባቸው አላስቀመጠም፤ ይህ ደግሞ በማንኛውም ጊዜ አልያም ውርሱ እስከተከፋፈለበት ጊዜ ሊሆን እንደሚችል መረዳት ይቻላል። በአጭሩ እንደዚህ አይነት የይርጋ ሥርዓት አለመኖር የውርስ ሂደቱን ከማንዛዛቱም ባለፈ በወራሾች መካከል አላስፈላጊ ግጭቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል። በመሆኑም ሕጉ ይህን ዓይነት ጥያቄ ማቅረቢያ ጊዜ ገድብ በግልፅ ማስቀመጥ አለበት።

5. የጉዲፈቻ ልጅ ውርስን በተመለከተ ሟቹ የጉዲፈቻ ልጅ በሚሆንበት ወቅት ውርሱን የሚወስድ ተወላጅ በማይኖርበት ጊዜ ወደ ወላጆች እንደሚሄድ ይታወቃል፤ በዚህን ጊዜ ወላጅ ሲል የትኛውን ነው? የዋናዎቹ

(የስጋ) ወይንም የጉዲፈቻ እናትና አባቱ ወይንስ ሁለቱን፣ በህጉ ላይ በግልፅ አልተቀመጠም።ስለሆነም የጉዲፈቻ ልጅ ውርስን በተመለከት ህጉ ፍትሃዊና አግባብነት ያለው አሰራር በመዘርጋት በደረጃ የጉዲፈቻውን ቤተሰብ ባስበለጠ መልኩ ሁለቱም ቤተሰቦች ሊወርሱ የሚችሉበትን አካሄድ በግልጽ ቢያስቀምጥ።

6. የባልና ሚስት መወራረስን በተመለከተ በእኩል ምናልባትም በህይወት ያለው ባል ወይም ሚስት የበለጠ የንብረት ወይም የሀብት ማፍራት ሂደት ውስጥ ተሳታፊ ሊሆን በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ አትውረስ ማለትና በዚህ ሂደት ውስጥ ምንም ቀጥተኛ የኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦ የሌላቸውን ሰዎችና መንግስትን በቅድሚያ መጋበዝ በጣም ተገቢነት የሌለው ሥርዓት እንደሆነ ማየት ይቻላል። በሀገራችን ካለው ጥብቅ ቤተሰባዊና ማህበራዊ እሴቶቻችን በመነሳት የባልና የሚስት እርስ በእርስ የመወራረስ ጉዳይ የሚያጠያይቅ ጉዳይ አለመሆኑን ነው። ከዚያ ይልቅ በየትኛው የወራሽነት ደረጃ ላይ ይቀመጡ የሚለው ዋናው ጥያቄ መሆኑን በመረዳት ጉዳዩን ከአገሪቱ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችና ልማዶች በመመርኮዝና የተለያዩ አማራጮችን በመመልከት መወሰኑ አስፈላጊ ነው። ባልና ሚስት በጋራ ያፈሩትን ንብረት የሟች የውርስ ሀብት አድርጎ አንዱን በማግለል በጋራ ካፈሩት ንብረት እንዳይጠቀሙ ማድረግ ማህበራዊ ግምት ውስጥ ካለማስገባቱም በላይ ከቤተሰብ ሕጉ ጋር የሚጋጭ ነው።

7. ሌላው በሕጋችን ቦታ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ በጋብቻው ውስጥ መሰረታዊ የጋራ የቤት እቃዎችን በሚመለከት ሲሆን እነዚህን ከፍተኛ ዋጋ ሊያወጡ የማይችሉ መገልገያ እቃዎች ይህ ሰው በህይወት እስካለ እንዲጠቀምባቸው በግልፅ ሊፈቅድ ይገባል።

8. በኑዛዜ የሚደረግ ውርስ በተመለከተ በህጋችን በግልፅ የተቀመጠ የኑዛዜ ትርጉም አለመኖሩ የሕጉ አተገባበር ላይ ችግር እንዳላስከተለ ቢታወቅም ኑዛዜ ለሚለው ሀሳብ በግልጽ ትርጓሜ ማስቀመጡ በሕጉ ውስጥ ያሉ መርህና ድንጋጌዎችን በቀላሉ ለመረዳት ያግዛል፡፡

9. የምስክር ብዛት እና የቀንና ፊርማ አፃፃፍን ስናይ በሕግ ቁጥር 887 ተናዛዡ የሚቀመጡ ቀኖች፣ የምስክር እና የአዋዋይ ሰራተኛው በአጠቃላይ በአንቀፅ 881(3) እና 884(3) መሠረት በግልፅ እና በተናዛዡ ፅሁፍ የሚደረጉ ኑዛዜዎች ሲደረጉ በእያንዳንዱ ወረቀት ላይ ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ገፅ ላይ እና በየገፁ መጨረሻ/ስር/ ላይ ፊርማ እና ቀን እንዲደርግ በግልፅ የሚያስገድድ ድንጋጌ መሆን ይገባዋል፡፡ክብደት ሊሰጣቸው የሚገቡ ፎርማሊቲዎችን በማጠናከር እና በኑዛዜው ህልውና ላይ ወሳኝ ያልሆኑትን ቀሪ በማድረግ የማሻሻል ስራውን ማከናውን ይቻላል፡፡የኑዛዜ ማድረጊያ ሥርዓቶችን ለአካል ጉዳተኞች በሚመች መልኩ ሲዘጋጁ በአካል ጉዳታቸው ባህሪ ምክንያት ለመጭበርበርና መታለል የተጋለጡ ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት ቀላል ነው፡፡ ስለሆነም አካል ጉዳተኞች የሚያደርጓቸው ኑዛዜዎች ግልፅ ኑዛዜ በተለይም ኑዛዜ ለመቀበልና ለማረጋገጥ ስልጣን በተሰጠው ተቋም(notarial will) ፊት እንዲሆን ማድረግ የኑዛዜው ቃል የአካል ጉዳተኞች የራሳቸው መሆኑን ለማጠራት ስለሚያግዝ እነዚህን መሰል አጋጣሚዎች በማስቀረት የአካል ጉዳተኞችን ኑዛዜ የማድረግ መብት ለመጠበቅ ዓይነተኛ ሚና ስለሚጫወት እነዚህን ልምዶችን አሰራር ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ እንዲስተካከል ቢደረግ መልካም ነው፡፡

10. በውርስ ሕጋችን የተቀመጠው የአራት ምስክሮች አስገዳጅ ድንጋጌ የተጋነነ ነው፤ ስለዚህም በምስክሮች ፊት የሚደረግ የፅሁፍ ኑዛዜ በአገሪቱ የተለመደውን አሰራር ተከትሎ በመተግበር ከአራት ወደ ሶስት

እንዲወርድና እንዲሻሻል መደረግ አለበት፡፡በተለይም ከ23 አመት በታች ላሉ ለህፃናት ትኩረት ተሰጥቶት አስፈላጊው ማሻሻያ ሊደረግበት ይገባል፡፡

11. የኢትዮጵያ የውርስ ህግ አቋም አስገዳጅ የውርስ ድርሻን አለማስቀመጡ ከሲቪል ሎው ይልቅ ከኮመን ሎው ሕግ ሥርዓት ጋር የመቀራረብ ባህሪ እንዳለው የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ሥርዓት አለመኖሩም ወራሾች በተለይም ተወላጆች ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸውን አጥተው ለጥገኝነትና ለማሕበረሰቡ ሸክም እንዲሆኑ ምክንያት ከመሆኑም ባሻገር የውርስ መብትን ላለማጣት በሀሰት በሚዘጋጁ ኑዛዜዎች መነሻነት ለሚፈጠሩ ክርክሮች መንስዔም ይሆናል፡፡ አስገዳጅ የውርስ ድርሻን ማስቀመጥ የአውራሹን መብት በመገደብ የወራሾችን ውርስ መብት የመጠበቅና ልጆች በወላጆቻቸው አማካኝነት ወደዚች ምድር የተቀላቀሉ መሆናቸውን ከግምት በማስገባት ቤተሰብ ለልጆች ያለበትን ኃላፊነት ለማጠናከር ፋይዳው የጎላ ከመሆኑም በላይ ከውርስ ተነቅለናል በሚል ምክንያት ወደ ፍርድ ቤት የሚመጡ በርካታ ክርክሮችን ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡

12. ከኑዛዜ ነፃነት ጋር ተያይዞ ክፍተት አለበት ተብሎ የተጠቀሰው ከውርስ መንቀልን የተመለከተው የሕጉ ክፍል ነው፡፡የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 938(3) ይዘት ሊሰረዝና ከውርስ የተነቀለው ሰው የቀረበበትን ምክንያት እንደምክንያቱ ይዘት በማስረጃም ሊያስተባብል የሚችልበትን እንዲሁም ፍርድ ቤቶችም የምክንያቱን እውነታነት ሊመረምሩ በሚያስችላቸውና የተቋቋሙበትን ዓላማ ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ሊሻሻል ይገባል፡፡

13. በአጠቃላይ ምንም እንኳን ከውርስ አጣሪ አመራረጥ ጋር በተያያዘ የውርስ ሕጉ ችግር ባይኖርበትም በአሰራር ደረጃ አጣሪዎችን የመምረጥ ሂደት ከሕጉ ዓላማ/መንፈስ እየወጣና እና በተወሰነ ዓይነት አሰራር

(በፍርድ ቤት ውርስ አጣሪዎችን በማስሾም) ላይ ብቻ የተመረኮዘ እየሆነ መጥቷል ማለት ያስችላል በሕጉ ሌሎች ዓይነት የውርስ አጣሪ የሚሆኑ አካላት ቢካተቱ የውርስ ማጣራት ስርዓቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ሊያደርገው ይችላል ለምሳሌ በሕግ የሚወሰኑ ለውርስ ማጣራትም ሆነ ንብረት ለማስተዳደር ዓላማ የሚቋቋሙ የመንግስት ተቋማት እንዲኖሩ ተደርጎ እነዚህ ተቋማት የውርስ አጣሪ የሚደረጉበት አሰራር ቢፈጠር ተቋማቱ የሕግ ባለሙያዎችን ብቻ ሳይሆን የሂሳብ እና የማኔጅመንት ባለሙያዎችንም ጭምር ሊይዙ ስለሚችል የውርስ ማጣራቱን ሂደትም ሆነ ውርስ ሀብት ማስተዳደሩን ሂደት ውጤታማና ቀልጣፋ የሚያደርገው ነው፡፡ይህም አሁን እየተሰራበት ያለውን እና በሕጉ በግልጽ እውቅና ተሰጥቶት ሊሰራበት ይገባል በማለት ከፍ ሲል እንደ አንድ አማራጭ ሀሳብ ያቀረብነውን ወራሾች ራሳቸው ከመካከላቸው የሚመርጡት የውርስ አጣሪ ውርስ ከሚያጣራበትም ሆነ ወራሾች በአጣሪነት የሚመርጧቸው ሌሎች ባለሙያ ያልሆኑ ሰዎች ውርሱን ከሚያጣሩበት እና ከሚያስተዳድሩበት ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር የተሻለ አማራጭ ይሆናል፡፡

14. ውርስ ወይም የኑዛዜ ስጦታን ላለመቀበል የሚያስፈልግ ችሎታ በሀገራችን ሞግዚቱ ለአካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የሚያገኘውን የውርስ ሀብት ለመተው እንዲችል ጉዳዩን ለፍ/ቤት አቅርቦ ማስፈቀድ አለበት በሚል ቢስተካከል ለአካለ መጠን ያላደረሱ ልጆችን መብት የበለጠ የሚያስጠብቅ ይሆናል፡፡ በፍትሀብሄር ህጉ 298 የተቀመጠውን "የቤተዘመድ ምክር ቤት ጉባዬ ካልፈቀደለት በቀር" የሚለውንም አገላለጽ ሊተካ ይችላል ብለን እናስባለን፡፡ እንደዚሁም ሌሎች በህግ ፊት ውጤት ያላቸውን ድርጊቶች ለመፈጸም ችሎታ እንደሌላቸው በህጋችን የተገለጹትን ግለሰቦችም ወደግምት ውስጥ ሊገቡ እና በተመሳሳይ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

15. የወራሽነት ማስረጃ አሰጣጥን በሚመለከት በፍትሐብሄር ሕጉ ቁጥር 996 ዳኞች ወራሽነት ምስክር ወረቀት መስጠት እንደሚችሉና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት ማረጋገጫ ዋስትና እንዲሰጣቸው ከወራሹ መጠየቅ

እንደሚችሉ ተቀምጧል፡፡አሁን ባለው አሰራር የሚስተዋለው ችግር የወራሽነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለመስጠት መሰማት ያለበት የማስረጃ ዓይነት ሲሆን ይህን በተመለከተ ምንም እንኳን በውርስ ሕጉ ወራሽነት ሰርተፍኬት ለማግኘት መሰማት አለባቸው ተብለው የተቀመጡ የማስረጃ አይነቶች ባይቀመጡም ፍ/ቤቶች ውሳኔ ከመስጠጣቸው በፊት በተግባር አስፈላጊውን ሁሉ የማጣራት ስራ የማድረግ ስልጣን እንዳላቸው በማመን የወራሽነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ከመስጠታቸው በፊት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ምስክሮችን በመስማት የአቤቱታውን ትክክለኛነት የሚያጣሩበት አሰራር ነበረ፤እንዲሁም የሌሎች ወራሾችና የሶስተኛ ወገኖችን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል በጋዜጣ እንዲወጣ በማስደረግ ሲሰሩ ቆይተዋል፤ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ወራሽነትን በቃለ መሃላ ብቻ በማስደገፍ እየወሰኑ ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን በማህበረሰባችን በአሁኑ ጊዜ ለቃለመሀላ የሚሰጠው ዋጋ እንደቀድሞው ጊዜ አለመሆኑ ተጨምሮ በርካታ የወራሽነት ማስረጃዎች በሀሰተኛ ቃለመሀላ አቤቱታ ምክንያት ወደግለሰቦች እጅ የገቡበትና ከሌሎች ወራሾች እውቅና ውጪ የውርስ ሀብቶች የተሸጡባቸው አጋጣሚዎች እና ያንን ተከትለው የተነሱ ክርክሮች በፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት ጭምር በተደጋጋሚ ተከስተው ትርጉም ተሰጥቶባቸዋል፤ በዚህም በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ የወራሽነት ማስረጃዎች በቀጥታ የውርሰ ሀብቱን ለመውሰድ በራሳቸው በቂ እንዳልሆኑ ተመልክቷል፡፡ በተለይም የሌሎች ሀገራትንም ሆነ የሀገራችንን የቀድሞ ተሞክሮ ማለትም ተቃዋሚዎች ካሉ ለማወቅ ይረዳ ዘንድ በጋዜጣ ማስታወቅን ጨምሮ ቢተገበር እውነተኛ ወራሾችን በመለየት ትክክለኛ መብታቸውን እንዲጠቀሙ ከማድረጉም በተጨማሪ የባለጉዳዮችንና ፍርድ ቤቶችን ጊዜና ወጪ እንዲቆጠብ፣ ሌሎች ወራሾችን ንቁ ተሳትፎና ሃላፊነት እንዲኖርባቸው ያደርጋል፡፡

16. አንድ ሰው በራሱ ቸልተኝነት ወይም ጥፋት የወራሽነት ማስረጃ ሳያወጣ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ የሚችል ሲሆን የይርጋ ጊዜ ደግሞ ቸልተኝነትንና ስንፍናን የመቅጣት ዓላማን ከመያዙ አንፃር ይህ በዚህ መልኩ ያለፈ ወይም

የባከነ ጊዜን በሙብቱ መስራት ካለመቻል ውስጥ ማካተት አግባብ አይደለም፡፡በመሆኑም በሙብት መስራት መቻልን ከአካለ መጠን መድረስ ጋር ማገናኘት ምክንያታዊና አግባብነት ያለው ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ይህ አተረጓጎም ከፍ ሲል ከተቀመጠው ምክንያት በተጨማሪ የራሳቸውን መብትና ጥቅም በአግባቡ ማስጠበቅ አይችሉም ተብለው በሕግ ግምት የተወሰደባቸውን ህፃናትን ከመጠበቅ አንፃርም ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

17. በሕጉ ቁጥር 1005(1) መሰረት የውርስ አጣሪው የሟቹን መሞት በሚከተሉ አርባ ቀኖች ውስጥ በውርሱ የሚገኙትን ንብረቶች በአንድ የእቃ ዝርዝር መዝገብ ውስጥ መጻፍ አለበትይህ ጊዜ የውርስ አጣሪው የውርስ ማጣራት ስራውን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ መታሰብ ይገባዋል በሚል ቢሻሻል የተሻለ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል እና ውጤታማ ይሆናል ብለን እናስባለን፤ አልያም አሁን ባለበት ሁኔታ ሟች ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ የሚታሰብ ከሆነም በድንጋጌው የተቀመጠው የ40 ቀናት ጊዜ ሊያሰራ በሚችል አግባብ ሊራዘም ይገባል ብለን እናስባለን፡፡

18. የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ከውርስ ሀብት ላይ ቀለብ መጠየቅ የሚችሉ ሰዎችን መጨመር ይቻላል፤አንደኛው አማራጭ ድንጋጌውን በሟች ላይ ጥገኛ የነበሩ ግለሰቦችን ባካተተ መልኩ እንዲቀመጥ ማድረግ ሲሆን የዚህ አማራጭ ችግሩ የሟችን ጥገኞች መለየት ሲሆን ፣ ተለይተውም በርካታ ከሆኑ የውርስ ሃብቱ እንዲጎዳ በማድረግ የወራሾቹን ጥቅም ሊነካ የሚችል እና በርካታ የቀለብ ጥያቄዎችን በማስተናገድ የውርስ ጉዳዩን እንዲጓተት ሊያደርግ መቻሉ ነው፡፡ ሌላው አማራጭ የሚሆነው በውርስ ሃብቱ ላይ የጎላ ጫና ሳይፈጠር የማህበረሰቡንም እሴት ከግምት ውስጥ በማስገባት በማህበረሰቡ ውስጥ ልዩ ቦታ ያላቸውን የቅርብ የቤተዘመድ አባላትን ባካተተ መልኩ በዝምድና ደረጃ ማስቀመጥ ሲሆን በዚህም ለምሳሌ ቀለብ መጠየቅ የሚችሉ የጋብቻን ዝምድና ጨምሮ ወደ ላይና ወደ ታች እስከ ሁለተኛ፣ ወደ ጎን እስከ ሶስተኛ የዝምድና ደረጃ ቢቀመጥ የተሻለ ይሆናል፡፡

19. በውርስ ክፍፍል ውስጥ ስለሚካተቱ ንብረቶች ስለ ውርስ ክፍያ በሚለው የሕጉ ክፍል ውስጥ ከፍትሀብሄር ሕግ ቁጥር 1060 ጀምሮ የውርስ ንብረት የሚከፋፈልባቸውን መንገዶች የሚያስቀምት ሲሆን ነገር ግን ሟች በህይወት ሳለ ከትዳር አጋሩ ጋር ሲጠቀምባቸው የነበሩ መሰረታዊ የቤት እቃዎች ለምሳሌ እንደ መቀመጫ፣ አልጋ፣ ቁም ሳጥን፣አልባሳት፣ የመመገቢያ እቃዎች፣ ምግብና ለምግብነት የተዘጋጀ እህል… ወዘተ ንብረቶች በውርስ ሀብት ክፍፍል ውስጥ እንደማይካተቱ የሚደነግግ ሕግ በሀገራችን የለምበመሆኑም ይህ ዓይነት የውርስ ሃብት ለክፍፍል በሚቀርብበት ጊዜ በህይወት የሚቀረው ተጋቢ እስከ እለተ ሞቱ ድረስ እንዲጠቀምበት ማድረጉ የዚህን ተጋቢ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህይወት የሚጠብቅ ሆኖ፤ ከሌላ የተወለዱ ልጆችን በተለይም ለአካላ መጠን ያልደረሱ ልጆችንም ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆን አለበት፡፡

20. ለኑዛዜ ስጦታ ዓይነቶች ግልፅና ዝርዝር ትርጉሞች ማስቀመጥ አሁን ላይ በሕጉ አተረጓጎም ወቅት እያጋጠሙ ላሉ በርካታ ጉዳዮች ተገቢ መፍትሄ ይሆናል፡፡

21. የመንፈስ መጨን በውርስ ሕጉ በቁጥር 868 በመንፈስ መጫን ምክንያት የተደረገ ኑዛዜ ፈራሽ እንደሚሆን ያትታል፡፡ በመሆኑምይህን አገላለፅ ግልፅና ቀጥተኛ እንዲሆን በተለይም ከእንግሊዝኛው ቅጂ ጋር ተመሳሳይ ሀሳብን እንዲያስተላልፍ ቢደረግ መልካም ነው፡፡

22. በስህተት የተጻፈ ቀን ይህ ጉዳይ በትክክለኛ መንገድ የተፃፈና በውጤታመነቱ ላይ ምንም ጥያቄ የማይነሳብት የኑዛዜ አይነት ላይ በመሆኑ ‘ሃሰት’ የሚለው ቃል ‘ስህተት’ ወደ ሚል መቀየር ይገባዋል፡፡

23. ውርስ ማጣራት በውርስ ሕጉ ወራሽነትን ስለማጣራት በሚለው ክፍል ውስጥ 'ውርስ ማጣራት' የሚለውን ሀሳብ 'ሂሳብ ማጣራት' በሚል ሲጠቀም ይታያል(ለምሳሌ ሕግ ቁጥር 962-969፣ 1052-1058)። በዚህ ቋንቋ አጠቃቀም/ሂሳብ ማጣራት/ መሠረት የውርስ ማጣራትን ተግባር የሂሳብ ስራ ብቻ ያስመስለዋል።በአንዳንድ ድንጋጌዎች ሂሳብ ማጣራት በሚል የተቀመጡ ሀሳቦችን ውርስ ማጣራት በሚል መተካት ይኖርበታል።

24. ርስት የሚለው ቃል በውርስ ሕጉ ውስጥ በጥቂት አንቀፆች ውስጥ ተጠቅሶ የሚገኝ ሲሆን በመሬት ፖሊሲ መሠረት የመሬት ርስትነት ወይም የመሬት ባለቤትነት ፅንሰ ሀሳብ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ርስት የሚለው ቃል ከድንጋጌዎች ሊወጣ የሚገባው ቃል ነው።

25. በፍታሐብሄር ቁጥር 1054 ውስጥ በሟች ላይ ገንዘብ ያላቸው ሰዎች ውርሱ ከተዘጋም በኋላ ቢሆን ከወራሾች ላይ መጠየቅ እንደሚችሉ የሚያሳይ ነው። የድንጋጌው ዋና ሀሳብ አውራሹ ላይ ገንዘብ ባላቸውና እና ወራሹ ላይ ገንዘብ ባላቸው ሰዎች መካከል የቀደምትነት መብትን ለመወሰን የተቀመጠ በመሆኑ የወራሹ የራሱ ባለእዳዎች የሚለው አገላለፅ "የወራሹ የራሱ ባለገንዘቦች" በሚል መተካት ይኖርበታል።

26. የአባትን ለአባት የእናትን ለእናት ወገን ስለሚሰጥ የወርስ ሀብት ይህ ሀሳብ የተገለፀበት ድንጋጌ የፍታሐብሄር ሕግ ቁጥር 849 ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት ከአንድ ወገን(ከእናት ወይም ከአባት ወገን) በውርስ ወይም በስጦታ መልኩ የመጡ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ለሌላኛው ወገን በርስትነት መስጠት እንደማይቻል ነው። አብዛኛው የጥናቱ ተሳታፊዎቹ ይህና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ጊዜ ያለፈባቸውና ማህበራዊ ስርዓታችንን ከግምት ያላስገባ በመሆኑ በሕጉ ውስጥ መቀመጥ የለባቸውም ብለው ያምናሉ። በአጠቃላይ

ይህ አይነቱ የእናት ለእናት ወገን የአባትን ደግሞ ለአባት ወገን የሚለው አሰራር አሁን ያለውን የማህበራዊ እሴት እንዲሁም ቤተሰባዊ ግንኙነት ጋር የሚፃረር ነው፤ በተጨማሪም በተግባር እየተሰራበት የማይገኝና በማህበረሰቡ ተቀባይነትን ያጣ አሰራር ነው ማለት ይቻላል። በመሆኑም ከዚህ ከአንድ ወገን የመጣ ንብረት ላይም በርካታ ገንዘብ ከዚሁ ንብረት ጋር እያካተተና እያሳደገ የሄደውን ሀብት ለአወረሰው ወገን ብቻ ይስጥ መባሉ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ይህ የሕግ ቁጥርና ተከታዮቹ ሁለት ድንጋጌዎች ሊቀሩ ወይም ሊሰረዙ የሚገባቸው ናቸው።

27. ተስካር የሚለው ቃል የተጠቀሰው በፍታሐብሄር ሕግ ቁጥር 1015(2) ውስጥ ሲሆን ቃሉ በኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሃይማኖት ስርዓት መሰረት አንድ ሰው ከሞተ በኋላ በተለያዩ ጊዜያት እርሱን በማስታወስና በማሰብ ከፈጣሪ ምህረት የሚለመንበት ሃይማኖታዊ ስርዓት ነው። በዚህ ዓላማ ቢቀመጥም በሌሎች እምነቶች ለምሳሌ በእስልምና እና ካቶሊክ እምነቶችም ተመሳሳይ ስርዓት እንዳለ ለማወቅ ተችሏል። በመሆኑም አንድም በአሁኑ ጊዜ ካለው ነባራዊ የፖለቲካ ስርዓት አንፃር የአንድን ማህበረሰብ ስርዓት ብቻ የሚመለከት ድንጋጌ ማውጣት አስፈላጊ ባለመሆኑ እንዲሁም ካስፈለገም የዚህ ቃል ትርጉም በተመሳሳይ ድንጋጌ ውስጥ 'ለሟቹ መታሰቢያ የሚደረገው ወጪ…' በሚል በተብራራው ሃረግ ውስጥ ሊሸፈን የሚችል ስለሆነ የቃሉ መጠቀስ አስፈላጊ ባለመሆኑ ቢወጣ የተሻለ ነው።

28. የሟችን ባለገንዘቦች እና የኑዛዜ ተጠቃሚዎችን ስለማሳወቅ በሕጋችን ቁጥር 1018(1) ስር እንደተቀመጠው ሟቹ እዳ እንዳለበት የሚያሳይ ሁኔታ ካጋጠመ ወይም ከተገመተ አጣሪው ጠቃሚ መስሎ በሚታየው ቦታ ላይ ባለገንዘቦችን ለማሳወቅና ለመጥራት ማስታወቂያ እንዲያወጣ ያዝል። በዚህ ግለሰቦች ከአካባቢያቸው አልፈው በተለያዩ እጅግ ርቀት ባላቸው ቦታዎች ላይ ሆነው በሚኖሩበትና የንግድ ልውውጥ በሚያደርጉበት ዘመን ይህንን ኋላ ቀር አሰራር መከተል ከነባራዊ ሁኔታው መራቅ ሲሆን የባለ ገንዘቦችንም

ጥቅም እንደሚጎዳ አያጠያይቅም፡፡ ስለዚህም ይህን አሰራር ሕጋዊ ድጋፍ በመስጠት ስራው በፌደራል እና በክልል በመንግስታዊ(በፌደራል እና በክልል) ጋዜጦች በኩል እንዲሰራ ቢደረግ ፍትሃዊ አሰራርን ከማስፈኑና የባለገንዘቦችን ጥቅም ከማስጠበቁም በላይ የችሎት መዳተትንም ይቀንሳል፡፡